Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto
ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ
1910 Kennedy Road, Unit 3, P. O. Box 417, Toronto, ON, M1P 2L8 E-mail:

# የ ፍኖተ ሳተላይት ሬድዮ ሐተታ: <u>የቄስ ነጋዴ ይሆናል ወንበዴ፤ ይሆናል ሰዊሮስ</u>

***በዘረኝነት ተጠፍሮ***
***የተጫነ አህያ!***
***አትቀስቅሱኝ ይላል***
***ተጋድሞ ጅብ ጉያ*** !!!!

ኢትዮጵያ የመቻቻል ሀገር የሆነችው ዛሬ ወይም ትላንት አይደለም_ ረጅም ታሪከን አስቆጥራለች፤ በሀይማኖታቸው ምክንያት ተጠቅተው የተሳደዱትን ሳይቀሩ ተቀብላ አስተናግዳ የማይፋቅ ታሪክ አጽፋለች፡፡ ስለ ፍቅር በስመአብ ይቅር ያለችም ሀገር ናት እንጂ ሀይማኖትን እንደ ጅማት አክርራ ጠብ ግጭትን ያለች አልነበረችም፤ አይደለችም፡፡ በአንጻሩ ዘረኛ ባለጌዎች ሆኑ ፋሺስት ሶላቶዎች ግን ሀይማኖትን ምክንያት አድርገው ሀገር ሊከፋፍሉና ሊያጠፉ ሞክረው ነበር፡፡ ወያኔም ኮለኔሉም ጸረ ኢትዮጵያ፤ ጸረ አንድነት በመሆናቸው የአንድነት ነጸብራቅ ሆና የቆየችውን ቤተ ክርስቲያን ለማውደም ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም፡፡ ጥራዝ ነጠቁ፤ ግራ ነኝ ባዩና ግራ የተጋባው ደርግም ቢሆን ባለው አቅም ጸረ ቤተክርስቲያን ነበር፡፡ ህዝብን ግን ሀይማኖቱን ሳያስደፍር ቆይቷልና የዛሬው ሴረኞች ጥቃት እንዲሁ የሚከሽፍ መሆኑ አያጠራጥርም፡፡

የብሄር እኩልነት ጥያቄ የተነሳው በዘፈቀደ ወይም አንድ ዋለልኝ የተባለ ዜጋና ትውልዱ ሥራ ሲያጡ ያነሱት ጉዳይ አይደለም፡፡ ለሀገር ለለውጥ ጠንቅ እየሆነ በመምጣቱና ተራማጅ ክፍሎች ድብብቆሽ ትተን ፊት ለፊት ተጋፍጠን መፍትሄ እንስጠው ብለው የጣሩትን ሚመለከት ነው፡፡ የራስን ዕድል በራስ መወሰን ሲሉም፤ በነበራቸው ርዕዮት መሰረት መብትን አውቆ አንድነትን በዴሞክራሲ ማጽደቅ በሚል እንጂ በጎጥ እንሸንሽን በሚል ሥርዓተ አልበኝነትም አልነበረም፡፡ ጠባቦች መርሁን በአሉታዊ ለጥጠው መገንጠል፤ ሁሌም መገንጠል ብለው ስህተታቸውን ሊያሰፍኑ ቢጥሩም ሀቀኛ መፍትሄ ፈላጊዎቹ_ እነ ዋለልኝ ጭምር_ ግንጠላን ከቶም ለሰኮንድ አላቀነቀኑም፡፡ ሀቁ ይህ ነው፤ ይኸው ከ 50 ዓመት በላይ ኢህአፓ የሀገር አንድነት ብሎ፤ ገንጣዮችን ተጻሮ ሲታገልና መስዋዕትነትንም ሲከፍል ቆይቷል፡፡ ይህንን ሊል የሚችል ሌላ ማንም ሀይል የለም፤ ሁሉም ተጎንብሰዋል፤ ለሹመት ሲሉም ተሞዳምደዋል። ጨቋኝን፤ ገንጣይን ሙሴ ብለው በታሪክ መድረክ ቆሽሸዋል፡፡ ዛሬ ግን ታሪክ በራዦችና ከላሾች መደረክ አጨናንቀው ሀሰት ሀቅ ነኝ ብላ፤ ልብወለድ፤ እውን የነበረ የሆነ ተብሎ፤ የኢህአፓ መስራቾችና ተራኪዎች ከመአሸን ፈልተው ድብልቅልቁ በወጣበት ጊዜ ላይ ደርሰናልና ነጋ ጠባ ሀቁ ይህ ነው ብለን ማቅረቡ የግድ ሆኖ ይገኛል፡፡ ሳዊሮስ የዲያብሎስ ሎሌ እንጂ ጳጳስ የሚያሰኝ የዶሮ ያክልም አጥንት የለውም፡፡ ሲኖዶሱ ላይ የመጣው ጥቃት የአገዛዙ ነው፤ የሀገር ማፍረሱ ዕቅድ ዋና አካል ሴራ፡፡ ዘረኛው ቄስ በራሱ የወጠነው አይደለም። ባለሜንጫውም፤ ኮለኔሉም

አቅደው የገፉት ነው፡፡ አንድነትን ለማፍረስ ቤተክርስቲያንን ማፍረስ፤ አማርኛ ቋንቋን በጉራማይሌ ይዘት ማሳጣት፤ ታሪክን መካድና አኖሌያዊ ይዘት ማላበስ፤ እርያን በሬ ማለትን ማስፈን ብለው አምርረው እየሰሩበት ነው፡፡ አደብ ገዝተው ተሳሳትን ብለው የሚመለሱ ሳይሆን ኮለኔሉ የህዝብን ሀይማኖት ሰለጠንኩ ብሎ ሲዘልፍ እንዳረጋገጠው የሚቀጥሉበት ነው፡፡ ከወዲሁ ህዝብ  ሀገር ሀይማኖቱን ለማስከበር ቆርጦ መታገል፤ ትግሉን መቀጠል አለበት እንጂ ዕርቅ ገለመሌ ብሎ እጆቹን ማጠፍ፤ ሰይፉን አፎቱ መከተት አይጠበቅበትም፡፡ ሀገራችን በተቃውሞና አድማ መናጥ አለባት፤ የሰይጣን ልጆች ይውደሙ መባልም ይኖርበታል፡፡

የድርሻቸውን ተወጥተው ባለፉ ሰዎች ላይ የሚባለውና የሚጻፈው ሀሰት በርክቷል፡፡ ወያኔዎችም ምድር አንቀጠቀጥን ብለው ሀሰት በኩንታል ሲጭኑብን እንደነበር አልረሳንም፡፡ ሸንፈታቸውን አልቀበል ብለውም ዳግም ሊያንሰራሩ በአሜሪካ ታግዘው እየጣሩ ናቸው፡፡ ሲያምራቸው ይቀራል የምንለው ነው፡፡ ታሪክና ሀቅ ሚነጣጣሉ አይደሉም፡፡ ዘንድሮ ግን ፍቅር ብለው ጥላቻን የሚያራግቡ የሚያናፍሱ ከበዙበት ወቅት ደርሰናልና ጥላቻንም አለማመን ብልህነት ሊባል ደርሷል፡፡ ሰዉም ሀፍረተ ቢስ እየሆነ ነውና ያልሆንከውን ነበርክ ሲሉት፤ ያልዋለበትን ጦርነት ሲተርኩለት፤ ውዳሴ ምስጋና ሲሰጡት ይገባኛል ብሎ ተቀባይ ሆኗል፡፡ እግዚኦ ያሰኛል! ትግላችን ሀቅን ወደ ቦታዋ መመለስን የሚመለከት ነው፡፡ የሀገር ታሪክ ከተካደ፤ ከተበረዘ የጸረ ኢትዮጵያ ሀይሎች ግብ ወደ ስኬት ይጓዝላቸዋል፡፡ ኦነግ፤ ወያኔ የኢትዮጵያን ታሪክ በሀሰት የሚያቆሽሹት አለምክንያት አይደለም፡፡ ሀገር ወዳዶችም ጸንተው ታሪክን ለመጠበቅ ዘብ ይውጡ ስልን የቆየነውም እንዲሁ በምክንያት ነው፡፡ ዝም ካልናቸው ሀይማኖት ሀገርን በቀላሉ ያፈርሳሉ፡፡ ማፈናቀል ብቻ ሳይሆን ሀገር ቀምተው ለስደት ይዳርጉናል፡፡ ፍልስጤም አንሆናለን፡፡ ሌላ ድግስ የላቸውም ለእኛ፡፡

ዓይን ያለው ይይ ጆሮ ያለው ይስማ!!

ሀገር ታሪካችንን እንጠብቅ !

ዘረኛው አገዛዝ በጋራ በትግላችን ይውደም !

ቡትቶ ባንዲራዎች ይቃጠሉ!!